# የቅንጅት መኢአድ ድጋፍ ድርጅት በካናዳ

በካናዳ የሚገኘው የቅንጅት መኢአድ ድጋፍ አካል በአገራችን በኢትዮጵያ ሰላምና ዲሞክራሲ እንዲሰፍን፣ የሕግ የበላይነት እንዲኖር፣ ሕዝብ የመረጠው መንግስት እንዲመሰረት:አገራችን ከድህነትና ከኋላ ቀርነት ተላቃ እንድታድግ: እንድትበለጽግ ለሚደረገው ትግል ከወገኑ ጎን በመቆም የሞራል፣ የገንዘብና የሃሳብ እንዲሁም በዲፐሎማሲው መስክም ያላሰለሰ ጥረት ለማድረግ በአገር ወዳድነትና በፈቃደኛነት የተመሰረተ የድጋፍ ድርጅት ነው።

ከምርጫ 97 ምስረታ በፊት የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት /መኢአድ/፣ ቅንጅት ከተመሰረተ በኋላ ደግሞ የቅንጅት ድጋፍ አካል በመሆን በካናዳም በተለያዩ ከተሞች የድጋፍ ቻፕተሮች እንዲመሰረቱ በመርዳትና በማስተባበር ለምርጫ 97 ለቅንጅት የገንዘብ፣ የቁሳቁስ፣ የሞራልና የሃሳብ ድጋፍ አድርጓል። ከምርጫው በፊትና በምርጫውም ወቅት “አንድነት” እና “የኢትዮጵያ ድምጽ” የተሰኘ ጋዚጣም በቶሮንቶ አያተመ አሰራጭቷል።

የ1997 ምርጫ በወያኔ ሲጭበረበር፣ የሕዝብ ድምጽ ለማስመለስና ለማስከበር ለመብታቸው ሲታገሉ የተገደሉትን፣ የታሰሩትንና የተሰደዱትን ወገኖቻችንን በማሰብ፣ እንዲሁም የቅንጅት መሪዎች ቃሊቲ በታሰሩበት ወቅት እንዲፈቱ ከፍተኛ የተቃውሞ ሰላማዊ ሰልፎችን ሕብረተሰቡን በማስተባበር ሲያካሂድ፣ ለአለም መንግስታት ድምጹን ሲያሰማ፣ በምርጫው ሳቢያ በጎረቤት አገር የተሰደዱትን ስደተኞች በገንዘብ ሲረዳ፣ ትግሉን እንዳይዳከም የሚቻለውን ሁሉ ሲያደርግ፣ የቅንጅትን ትግል ለወያኔ ለማስረከብ ሲታገሉ የነበሩትን ሲያጋልጥና ሲታገል ቆይቷል።

በአሁኑም ጊዜ የቅንጅት መኢአድ የድጋፍ አካል ሆኖ አየሰራ ይገኛል። የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅትን /መኢአድን/ ዓላማና መርህ በመከተልም ይጓዛል። የተመሰረተበትን አላማ ከግቡ ለማድረስና የኢትዮጵያ ሕዝብ የድሉ ባለቤት አስከሚሆን ድረስ ትግሉን በጽናትም ይቅጥላል።

በካናዳ የቅንጅት መኢአድ ድጋፍ ድርጅት በውጭ አገር በድጋፍ ስጭነት ከተመሰረቱት መካከል ረጂም ታሪክ ያለውና አንጋፋ ድርጅት ነው። ዋናው ጽሕፈት ቤት በቶሮንቶ ካናዳ ይገኛል።

ቅንጅት የኢትዮጵያ የባሕልና የአርዳታ ድርጅት በቶሮንቶ